# የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ (SPS)
# በየቤተሰብ የትምህርት መብት እና ሚስጢራውነት ድንጋጌ (FERPA) ስር የተካተቱ መብቶች ማሳወቂያ እና አገልግሎት ላለመቀበል መፍልግዎን ማሳወቂያ ቅጥ

***በየቤተሰብ የትምህርት መብት እና ሚስጢራውነት ድንጋጌ (ፋሚሊ ኢዱኬሽናል ራይትስ ኤንድ ፕራይቬሲ አክት (FERPA) መሰረትይ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ታማሪዎች ወይም ዕድሜያቸው 18 ዓመት በላይ የሆነ "ተቀባይነት ያላቸው ተማሪዎች" ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪዎችን "የትምህርት መዝገብ" በሚመለከት አንዳንድ መብቶች ኣሏቸው። ተማሪው 18 ዓመት ካደረገ ከወላጆቹ ወይም ኣሳዳጊዎቹ ጋር እየኖረ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተማሪው ምሉ መብት ኣለው። መብቶቹ የሚከተሉት ናቸው:***

(1) የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የጽሑፍ ጥያቄ በቀረበለት በ45 ቀናት ውስጥ የተማሪውን የትምህርት መዝገብ የማያት እና የመመርመር መብት። .

(2) ተቀባይነት ያለው ተማሪው ወይም ወላጆቹ ቅኑ ኣይደለም፣ ኣሳሳች ነው ወይም የተማሪውን ምስጢር ኣሳልፎ ይሰጣል ብለው ያመኑበት የትምህርት መዝገብ እንዲሻሻል የመጠየቅ መብት። የሲያትል ፐብሊክ ስኩልስ መዝገቡን ላለምማሻሻል ከወሰነ ወዲያውኑ ለወላጆቹ ወይም ተቀባይነት ላለው ተማሪ ስለውሳኔ ያስውቃል። ከዚህ በተጨማሪም ውጤቱ እንዲሻሻል በተመለከት ያላቸውን ጥያቄ ወደ ቅሬታ ሰሚ ኣካል የማቅረብ መብት እንዳላቸው ይመከራል። ስለ ቅሬታ ኣቀራረብ ቅደም ተከተል የሚመለከት መረጃ ለወላጅ/ኣሳዳጊ ወይም ተቀባይነት ላለው ተማሪ ከውሳኔው ጋር ይሰጣል።

(3) በየቤተሰብ የትምህርት መብት እና ሚስጢራውነት ድንጋጌ (FERPA) ያለፈቃድ የተማሪው መረጃ እንዲለቀቅ ከመፍቀዱ በፊት በጽሑፍ የተማሪው መረጃ ትምህርት ቤቱ መረጃውን እንዲለቀቅ መፍቀዳቸውን የማሳወቅ መብት። ኣንድ ልዩ የሆነ የተማሪ መረጃ ያለፍቃድ መልቀቅ ሊያስከትል የሚችል ሁኔታ ለምሳሌ የትማሪውን መረጃ ተማሪውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ትምህርቱ ላይ ሊረዱት ለሚፈልጉ የትምህርት ቤት ባለስልጣናት መረጃውን መስጠት ሊሆን ይችላል። "የትምህርት ቤት ባለስልጣን" የሆነ በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ እንደ ኣስተዳዳሪ፣ ተቆጣጣሪ፣ መምህር ወይም ተባባሪ (የጤና ወይም የሕክምና ሰራተኛ እና ሕግ ኣስከባሪ) ሆኖ የተቀጠረ ሰው ሊሆን ይችላል። "የትምህርት ቤት ባለስልጣን" በተጨማሪ በጎ ፈቃደኛ ወይም የትምህርት ክልሉ እንዲያስተምር የትኮናተረው ኣገልግሎት ሰጪ ወይም የትምህርት ቤት ስራ እንዲያከናውን የትመደበ ሰው ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው የትምህርት ንብረት ኣጠቃቀም እና ክትትል ላይ በትምህርት ቤት ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር የሆነ ስራው ከተማሪዎች መረጃ ጋር የትሳሰሩ መረጃዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠይቅ ለምሳሌ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የህክምና ኣማካሪ ወይም ቴራፒስት፣ የኮሚቴ (ለምሳሌ ቅሬታ ሰሚ ወይም የስነስርዓት ኮሚቴ) ኣባል ሆኖ ለመስራት በጎ ፋቃደኛ የሆነ ወላጅ ወይም ተማሪ ወይ ሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣን ስራ ላይ የሚተባበር ወልጅ ወይም ተማሪ ሊሆን ይችላል። የትምህርት ቤት ባለስልጣን ተማሪው ትምህርቱን በሚመለከት ለመርዳት እና ሞያዊ ሓላፍነቱን ለመወጣት እስከሆነ ድረስ የተማሪውን መዝገብ የማየት ሕጋዊ የሆነ ስልጣን ኣለው። ተማሪው ኣዲስ ሊመዘገብበት ወይም የተመዘገበት ትምህርት ቤት በጠየቀው ግዜ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ፍቃድ ሳይጠይቅ የተማሪውን የትምህርት መዝገብ የማስተላለፍ መብት ኣለው።

(4) የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጉዳዩን በሚምለከት FERPA በሚያዘው መሰረት ካላየው ቅሬታቸውን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ዲፐርትመንት ኦፍ ኢዱኬሽን (የትምህርት ሚኒስትሪ) ቅሬታቸውን የማቅረብ መብት። የጽሑፍ ቅሬታ ወደ ሚቀጥለው ኣድራሻ፤ Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue S.W., Washington, DC 20202 መላክ ኣለብት።

***<u>የስም ማውጫ መረጃ፤</u>***

በFERPA መሰረት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ "የስም ማውጫ" መረጃ ኣስቀድማችሁ እንደማትፈቅዱ ካላሳወቃችሁ በቀር ለሁሉም የሚከተሉ (በነዚህ ብቻ ግን የተወሰነ ኣይደለም) የወላጅ-ኣስተማሪ ማህበራት፣ ለመገናኛ ብዙሃን፣ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች፣ ለሰራዊት (ሚሊታሪ)፣ የወጣት ማህበራት እና እስኮላርሺፕ የሚሰጡ ማህበራት ይለቃል። የሚመለከተ መረጃ የስም ማውጫ መረጃ ተብሎ ይታሰባል፤ ወላጅ/ኣስዳጊ እና የተማሪ ስም፣ የቤት ኣድራሻ፣ የቤት ስልክ ቁጥር፣ የቤት ኢሜል ኣድራሻ፣ የተማሪው ፎቶ፣ የተማሪው የልደት ቀን፣ የተመዘገበት ቀን፣ የትምህርት ደራጃ፣ የምዝገባ ሁኔታ፣ የተሰጠው ዲግሪ ወይም ሽልማት፣ የሚያጠናው ዋና የትምህርት ዓይነት፣ በወጉ የሚታወቁ የሚሳተፍባቸው እንቅስቃሴዎች እና ለኣትሌቶች የስፖርት ቡድን፣ ቁመት እና ሚዛን፣ በቅርቡ የተማረበት ትምህርት ቤት እና ሌሎች በጠቃላይ ጎጂ ናቸው ወይም የትማሪውን የግል መረጃ የማይተላለፉ ተብለው የማይታሰቡ መረጃዎች።

**<u>ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ 8ተኛ ክፍል (Pre-K to 8) ላሉ ተማሪዎች የስም ማውጫ መረጃ ስለመልቀቅ፤</u>**

የቅድመ መዋለ ህጻናት ተማሪ፣ የኣንደኛ ደረጃ ተማሪ ወይም የማሃከለኛ ደረጃ ተማሪ ወላጅ/ኣሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን የልጅዎ ስም የያዘው ማውጫ ይዘርጋ ኣይዘርጋ በሚለው ጉዳይ ላይ ሁለት (2) ኣማራጮች ኣልዎት። ኣንዴ ፎርሙን ሞልተው ለትምህርት ቤት ካስረከቡ ቡኋላ ምርጫዎ ኤሌክትሮኒካዊ በሆነ መንገድ ኮምፒተር ላይ ይሰፍራል። ይህ ሁለተኛ ኣዲስ ፎርም ሞልተው እስኪያስረክቡ ድረስ ኣይቀየርም። እባክዎ እታች ከተሰጡት ኣማራጮች ኣንዱን ሳጥን በመምረጥ ፎርሙን ወደ ልጃችሁ ትምህርት ቤት እስከ **ጥቅምት 10 (ኦክተበር 10)** ድረስ መልሱት። ወላጅ ወይም ኣሳዳጊ ይህን ፎርም መርጠው ፎርሙን ወደ ትምህርት ቤት ካላኩት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ኣለመመለስ እንደ ፍቃድ (ኣስቦ ሳጥን ሀ) ይወስዳል።

*Turn Over for Signature and Selection*

## ከቅድመ ማዋለህጻናት  እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች (Pre-K to 8):

እባካችሁ ኣንዱን በማክበብ ምረጡ፤

ሀ.  ስሙ እታች የተገለጸው ተማሪ በሚመለከት እላይ የተገለጸው የስም ማውጫ መረጃ እንዲለቀቅ ፈቅጃለሁ።

ለ.  ስሙ እታች የተገለጸው ተማሪ በሚመለከት እላይ የተገለጸው የስም ማውጫ መረጃ እንዲለቀቅ ሕግ ካላስገደ በስተቀ ኣልፈቅድም።

ምርጫዎ ለ ከሆነ – መረጃ ኣለቅም ካሉ፤ የልጅዎ መረጃ ታች የተዘረዘሩትን ክፍሎች ካላሟሉ በስተቀር በሚከተሉት ውስጥ ኣይካተትም። ከፈቀዱ፤ ፍቃድዎን ከሚከተሉት ተገቢውን በማክበብ ያመልክቱ።

**የሚዲያ (የዜና ኣውታር) መፍቀጃ**
ኣዎን፤ የሚዲያ (የዜና ኣውታር) ኣባላት ልጄን ትምህርት ቤት ግቢ ወይም/እና የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ዓላማው ለዜና እስከሆነ ድረስ ፎቶግራፍ እንዲያነሱት እና ኢንተርቪው ኣንዲያደርጉት ፈቅጃለሁ።

**የትምህርት ቤት መጽሓፍ (ይር ቡክ)/ የክፍል ፎቶ መፍቀጃ**
እዎን፤ የልጄ ፎቶ እና ስም የትምህርት ቤት መጽሃፍ እና የክፍል ፎቶ ላይ እንዲገባ ፈቅጃለሁ።

**የሁሉም ቤተሰቦች የእድራሻ ማውጫ (መዝገብ)**
ለሁሉም ቤተሰቦች፣የትምህርት ቤት ሰራተኞች እና የወላጆች ማሕበር (PTSA) እንዲሰጥ ፈቅጃለሁ።
ኣዎን፤ የኛ መረጃ (ቴሌፎን፣ ኣድራሻ እና ኢሜል) መዝገቡ ውስጥ ይግባ።

**የክፍል የወላጆች መዝገብ**
ለሁሉም ቤተሰቦች፣የትምህርት ቤት ሰራተኞች እና የወላጆች ማሕበር (PTSA) እንዲሰጥ ፈቅጃለሁ።
ኣዎን፤ የኛ መረጃ (ቴሌፎን፣ ኣድራሻ እና ኢሜል) መዝገቡ ውስጥ ይግባ።

**ድህረገጽ/ማሕበራዊ መገናኛ**
የተማሪው ፎቶ ወይም ቪዲዮ የትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ክልሉ ድሕረገጽ ላይ እንዲወጣ ፈቅጃለሁ። ስም ኣይጠቀስም። ኣዎን፤ የልጄ ፎቶ ወይም ቪዲዮ የህዝብ ድሕረገጽ ላይ እንዲወጣ ፈቅጃለሁ።

የህዝብ መዝገብ የሆነ ፋይል የመጠየቅ መብት የሚመለከት ማሳሰቢያ።

በዋሽንግተን ሕግ RCW 28A.320.160 መሰረት የትምህርት ክልሎች ወላጆችን/ኣሳዳጊዎችን በዋሽንግተን የህዝብ መዝገብ ድንጋጌ (Washington Public Records Act (RCW 42.56)) መሰረት የትምህርት ቤት ሰራተኛ የሰነስርዓት ውሳኔ መዝገብ ለማየት የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ማሳወቅ ኣለባቸው። ከሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የህዝብ መዝገብ የሆነ ፋይል ለመጠየቅ የጽሑፍ ጥያቄ ወደ፤ Office of the General Counsel: Attn: Public Records Request; SPS: MS 32-151; PO Box 34165: Seattle, WA 98124 መላክ ይችላሉ።

| **የተማሪው ምሉ ስም (በሚነበብ ሁኔታ የተጻፈ)** | **የተወለደበት ቀን** | **የተማሪው የትምህርት ቤት መታወቂያ ቁጥር** |
|---|---|---|

| **የፈራሚው ሰው ምሉ ስም ጻፉት** | **ወላጅ/ኣሳዳጊ/ዕድሜው የደረሰ ተማሪ ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|

እባካችሁን ይህን ቅጥ በቀጥታ ወደ ልጃችሁ ትምህርት ቤት በኣካል በመሄድ ስጡ ወይም በፖስታ ላኩት።
ሲኣይትል ፓብሊክ ስኩልስ ውስጥ የሚማሩ ከኣንድ በላይ ልጆች ካልዎ ለሁሉም የየራሳቸው ፎርም ሞልተው ወደየ ትምህርት ቤታቸው ላኩ።

ይህ ቅጥ ልጅዎ ትምህርት ቤት ከልጅዎ ፋይል ጋር ተሰንዶ ይቀመጣል።